# የሁለት ሺሕ ዓመቱ ፍጻሜ የደግ ነገር ሁሉ ፍጻሜ እንዳይሆን

ሁላችንም ለወገኖቻችን ቅርሶቻችን በመዝረፍና በማሻገር ሀገራችንን ከጽዮንነት አናውጣት እንበላቸው:: ሰውም ካልሡማ አባቶች ሆይ እንደ ነቢዩ እንደ ኤርምያስ አደራውን ለምድራችን ስጡ ልን:: ምድር ሆይ አንቺም እንደ ኢየሩሳሌም አባክሽን ንዋያተ ቅድሳቶቻችንን ከባቢሎን ምርኮ /ከአሕዛብና ከመናፍቃ ምዝበራ ከይሁዳም ስርቆት/ ሰውሪልን እንበላት::

ከዚህ ሁሉ በላይ እያሳሰበን ያለው ግን ከሁለም አቅጣጫ የሚጐስመው የማንአለብኝነት ነጋሪት የመቻቻልንና አብሮ የመኖሩን ባሕል እየሸረሸረውና ትርጉም እያሳጣው መሔዱ ነው:: በተለይ በአሁኑ ሰዓት ከላይ ቀደም ብለን ከጠቀስናቸው አካላት በመጀመሪያዎቹ በሁለቱ እየተፈጸመ ያለው ጉዳይ አስቸኳይ መፍትሔ የሚያሻው ነው:: መስቀል አደባባይ ለጸረ መስቀል ኮንፈረንስ የሚፈለግበት ምክንያት መቻቻልን ለማጥፋት ካልሆነ ለምን ሊሆን ይችላል? ቤተ ክርስቲያን አካባቢ ሆን ብሎ ሒዶ መጮኸና መረበሽስ ምን ዓይነት ነገር መሻት ነው? እነዚህንና ሌሎቹንም ሁኔታዎች ስናያቸው የሁለት ሺሕ ዓመቱ መጨረሻ የመቻቻልና አብሮ በሰላም የመኖር ባሕል መጨረሻም እንዳይሆን ያሰጋል:: ለዚህ ደግሞ ሐላፊነት የሁሉም አካላት እንጂ የመንግሥት ብቻ ወይም የእምነት ተቋማቱ ብቻ አይመስልም:: ለዚህ የሚያስፈልገውን ሁሉ በማድረግ የሁለተኛው ሺሕ ዓመት ፍጻሜ ችኩልነት፣ ጠብ አጫሪነት፣ እና ጸብና ግጭት የሚዘገበት እንጂ መቻቻልና ተግምኖና ተከባብሮ መኖር የሚፈጸሙበት እንዳይሆን ሁሉም ወገን ሓላፊነቱን ሊወጣ ይገባዋል እንላለን:: ው

***ወስብሐት ለእግዚአብሔር***

Mahibere Kidusan©2005, All Rights Reserved
አስተያየት ለመስጠት: webmaster@eotc-mkidusan.org